በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ቦሩ ሥላሴ፡- የስብከት ዘዴ

- ስብከት የሚለው ቃል ሰበከ አስተማረ፣ አዋጅ ነገረ ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ነው። በግሪክ፣ ኬሪግማ /kerygma / በእንግሊዝኛ /sermonl/ ይባላል። ተዛማጅ /ተመሳሳይ/ የሆነ ትርጉም አለው። ማስተማር አዋጅ መንገር የሚለውን የተረጉማሉ።
- የቤተክርስቲያን ዋናው ተልዕኮዋ ሰዎችን ከአለማመን ወደ ማመን ማምጣት፣ ያመኑትን ደግሞ በእምነታቸው ማጽናት ነውና። ስብከት የቤተክርስቲያን ትልቁ የአገልግሎት ክፍል ነው።

ማሳወቅ መለወጥ መመገብ በአለማዊም ሆነ በመንፈሳዊ ያልታወቀን ነገር ማሳወቅ ማስረዳት

ያልተረዱትን ማስረዳት ማልት ነው

ማስተማር መንፈሳዊ ምግብን ለሰዎች መመገብ ማለት ነው

ለአንድ ሰው ሥጋዊ ምግብ ለመመገብ ከሚያስፈልገው ዝግጅት በላይ ዝግጅት ያስፈልገዋል

የመልካም መምህር ባህርያት

- 1 በእምነት እና በእውቀት በመስተማር
- መንፈሳዊ መምህር ማስተማር ያለበት ብእምነት ነው እመነት የሌለው ሰው ሌላውን ሊያሳምን አይችልም ክህደትን ቆርጦ ለመጣል አስተማሪው በመጀመሪያ በእምነት መሳል አለበት
- መዝ 115 ፡1 አመንኩ በዘነበብኩ አመንሁ ስለዚህ ተናግርኩ
- ሌላው መምህር ሠወች የእግዚአብሔር ቸርነት እንዲቀምሱ የመጋበዝ ሀላፊነት እለበት
- መዝ 33 ፡ 15 ጠአሙ ወተአይምሩ ከመ ሐር እግዚአብሔር ነግር ግን ያልቀመሱትን ነገር ቅመሱ ማለት አይቻልም አንድ መምህር በእምነት ያላጣጣመውን ትምህርት ቢያስተመወር ትርፉ ድካም ብቻ ነው

ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ‹እንጸልይ ዘንድ አስተምረን› ብለው ለጠየቁት ሉቃ.11፡1 የተሰጣቸው መልስ አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር የሚለው የዘውትር ጸሎት ነው።ይህም ማለት ሰባኪው በየትኛውም ደረጃና ሁኔታ ውስጥ ቢሆንበሁሉም መንገድ ቃለ እግዚአብሔር የተማረ፣ ለመማር የተዘጋጀ፣ ሊሆን ይገባል። ‹ ብርጭቆ ካልሞላ አይፈስም› እንደሚባለው ሰባኪ ሙሉ የሆነ ነገር ከሌለው የምእመናን ልብ ማርካት አይችልም። እርሱም የሚናገረው ይጠፋዋል።ስለዚህ ከሌሎች መምህራን፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት፣ ከምቹ አጋጣሚዎችወዘተ መማር አለበት።

- ዮሐንስ አፈወርቅ ‹ለእመ ሐሰሰከ ትኩን መምህረ ኩን ግንዳሌ መጻሕፍት› ብሏል።

- ፍቅርን ልንይዝ ይገባል

ሠናየ ሀልዩ በልብክሙ/ ለቢጽክሙ/ ተፋቀሩ በኩሉ ጊዜ ዝ ወዕቱ ፈቃዱ ለእግዚአብሔር መንፈሰ ኢታጥፍኡ ተነብዮ ኢትመንኑ ወኩሎ አመክሩ ወዘሠናየ አጽንኡ‹‹ በልባችሁ መልካም ነገርን አስቡ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርስበርሳችሁ እንድንፋቀሩ ነውና እርስበርሳችሁ ሁልጊዜ ተፋቀሩ መንፈሳዊ ነገርን አታጥፉ ትንቢትንም አትናቁ ሁሉንም መርምሩ የተሻለውን አጽንታችሁ ያዙ›› ከዚህ ላይ እንደምነረዳው ቅዱስ ያሬድ ለፍቅር ከ---እስከ የሚባል የጊዜ ገደብ እንደሌለው ሁልጊዜ በማለት አስቀምቶልናል። ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም 1ኛ ቆሮ 13፡ 8 ገደብ ያለው የጾም ጊዜ እንጅ ለፍቅር ገደብ የለውም።

- ተፋቅሮ ኢያስተፄንስ ወኢያሄሊ ተድላ ለባህቲቱ ‹‹ ፍቅር ማንንም ችግር ውስጥ አያስገባም የብቻ ድሎትንም አያሳስብም ወይም ብቻየን ልደሰት አያስብልም›› ፍቅር ከስግብግብነት ከቀናተኛነት ወጥቶ ለሌሎች መትረፍ ስለሆነ ብቻየን ይድላኝ አያሰኝም። 1ኛ ቆሮ 13፡
- እመኒ አዕመርነ ነገረ ኩሉ ሰብእ ወነገረ መላእክት ምንት ይበቁአነ ለእመ ኮነ እሩቃነ እምተፋቅሮ

- 2. መጥኖ ማስተማር የሚችል መሆን አለበት
- ያልተመጠነ ነገር ይጎመዝዛል ያልተመጠነ ነገር ጣእም አይኖረዎም
- ቅዱስ ጴጥሮስ በአነደኛ መልእክቱ 4 ፡8 እና 5፡ 8 በመጠን ኑሩ ብሎ እንዳስተማረን ለሁሉም ነገር መጠንና ልክ እለው ዘበልአ በአቅሙ የሀድር በሰላም እንዳለው ጠቢቡ ሰሎሞን ስጋዊ ምግብን በመጠን እንደምንመገብ ሁሉ ቃለ እግዚአብሐየርንም በመጠን መማር ያስፈልገናል
- ምእመናን መመህሩ የያዘውን ሁሉ እንዲይዙ የሚሞክርባቸው ቤተ ሙከራወች አይደሉም በመጠን ሰምተው ከህይወታቸው ጋር እንዲያዋህዱ የሚጠበቁ ናቸው እንጅ
- ማር 4፡ 33 ወበዘ ከመዝ አምሳል ተናገሮሙ ቃሎ በአምጣነ ይክሉ ሰሚዓ ። መስማት በሚችሉበት መጠን እነዚህን በሚመስል በብዙ ምሳሌ ቃሉን ይነግራችው ነበር

- ክርስቲያናዊሕይወት
- ‹ወዘሰ ኢይከል ሠሪዐ ቤቱ እፎኑ ያስተሐምም ቤተ እግዚአብሔር› ጢሞ 3፡5 እንደተባለ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያገለግል ፣ ክርስቶስ የሰበከውን ቅዱስ ወንጌል የሚናገር አባቶች በቆሙበት የሰብከት ሰገነት የሚቆምና ምእመናንን ወደ እግዚአብሔር የሚጠራ ሰባኪ ሃይማኖቱ የቀና፣ ስነ ምግባሩ የተስተካከለ መሆን ይጠበቅበታል።

- .ራስንአለመስበክ
- ምንም እንኳን በሥልጣን፣ በፈቃድ፣ በሕልውና፣ በባሕርይ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ /ትክክል/ ቢሆንም በተዋሐደው ሥጋ ምክንያት ወልድ ከአብ ዘንድ የተላከና ለአብ የታዘዘ ነው። ‹ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን ላደርግ አልሻምና› በማለት እንደተናገርው።/ዮሐ 5፡30/
- መጥምቀ መለኮት ዮሐንስም ‹ ስለ ራስህ ምን ትላለህ› ብለው ለጠየቁት የሰጠው መልስ ‹ የጌታን መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምጽ እኔ ነኝ› ብቻ ነበር ያለው። /ዮሐ 1፡ 23/ ዮሐንስ የክርስቶስን ፈቃድ እንጂ የራሱን የሚያውቀውን እውነተኛ ታሪኩን እንኳን መናገር አልፈለገም።

- የሚያደንቁት ሰባኪና ምን ልሥራ ብለው የሚጠይቁት ሰባኪ በእጅጉ ይለያልና ሰባኪ ራስን ከመስበክ ነጻ መሆን ይጠበቅበታል።
- ‹ብዙ ሰዎች ቸርነታቸውን ያወራሉ የታመነውን ሰው ግን ማን ያገኘዋል› ምሳ 20፡6
- ‹እግዚአብሔር የላክው የእግዚአብሔር ቃለ ይናገራል› ዮሐ. 3፡34
- ‹ ልቡናዬ መልካም ነገርን አፈለቀ /አወጣ/ ዳዊት ፣ሕርያቆስ›
- ‹እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን› 1ቆሮ 1፡23 እንዲል እንደተባለ።

- የተሰባክያንንሥነልቡናመረዳት
- በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተሰባክያንን ስነ ልቡና ማወቅ ለስበከተ ወንጌል መስፋፋትና ውጤታማነት የላቀ አስተዋጽኦ አለው። ጌታችን በዚህ ምድር በነበረበት ጊዜ ውስጥ የተጠቀመበት ዘዴ የአድማጮችን የልብ ፍላጐት በጥልቀት መረዳት ነበር።
- ሊጠይቁት እንደፈለጉ ማውቀና መረዳት
- መዳን እንደሚወዱ ማወቅ፣ ጠይቆ መረዳት
- እንደራባቸውና ምግብ እንደሚያስፈልጋቸው መግንዘብ

- የስብከትሰዓትን መጠበቅ
- ሰባኪው ሰብከቱን ወጤታማ ለማድረግ በጊዜ መወሰን ግድይልዋል። የሚጠቀምባቸውን ጊዜያት ወስኖ ማክበርና በአገባቡ ሥራ ላይማዋል። ሰዓት ከረዘመ ሰበከቱ ሊንዛዛና አስልቺ ሊሆን ይችላል።ምእመናኑ የመደንዘዝ፣ የመሰላቸት የወሬ የእንቅልፍ ስሜትና አቋርጦ መሄድ ይፈልጋል።የስብከቱ ሰዓት ካጠረም የሚፈለገው መልእክት አይተላለፍም ሰማዕያኑ ይታወካሉ ጥያቄም ይፈጠርባቸዋል።መምህሩ እወቀት /ፍላጐት/ እንደሌለው ሊገመቱ ይችላሉ የስብከት ሰዓት እንደየሁኔታው ለመወሰን፡-
- ትምህርቱ የሚሰጥበት ቦታ፡- ቀዝቃዛ ፣ሞቃታማ፣ ዝናብ የሚበዛበት፣ ዝናብ ያልወቅቱ የሚዘንብበት
- ትምህርቱ የሚሰጠው ሜዳ ላይ ቤተክርስቲያን ውስጥ፣ አዳራሽ
- ትምህርቱ የሚሰጠወ ጧት፣ ከሰዓት፣ ማታ

- የስብከት ርዕስመጠበቅ
- ስብከት ርዕሱ ካልተጠበቀ ውጤታማ ሊሆን አይችልም፤ ምእመናኑ የሚጨብጡት ነገር አይኖራቸውም ሰባኪውም ትዝብት ውስጥ ይወድቃል።ርዕስ መጠበቅ የሚሰጠው ትምህርት ወጥና ያልተደባለቀ ያደርገዋል
- ለምሳሌ፡- ስለ ምሥጢረ ሥላሴ ጀምሮ ስለ ጾም
- ስለ ቅዱስ ቁርባን ጀምሮ ስለ ሥዕል
- ስለ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ጀምሮ ስለ ታቦት... የሚል ከሆነ ፥ አርባስድስት ጥዳ አንዱንም... አረረባት› እንደተባለው ይሆናል። ሰዓትና ርዕስ መጠበቅ የአንድ ሰባኪ መታወቂያዎች ናቸው።

- ዮሐ 16 ፡ 12 የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም በማለት ተነግጿል
- ግብር ዘአልቦ ምጣኔ ገአር ውእቱ ወለገአርኒ ይተልኦ ዝንጋኤ ልክ የሌለው ስራ ድካም ነው ድካምንም መዘንጋት ይከተለዋል ያልተመጠነ ትምህርትም ተናጋሪውንም ሰሚውንም ወደመሰልቸት ያደርሳል
- እብ 11፡ 32 ሁሉን እንዳልናገር ጊዜ ያጠረኛል
- ሐዋ 20 ፡ 9 ጳውሎስም ነገር ባስረዘመ ጊዜ አውጠየኪስ የተባለው ጎበዝ ከመስኮት ወድቆ እንደሞተ እናያለን ስለዚህ ነገር በመጠን ማስተማር እንደሚገባ ያስረዳል

- የስብከትዓይነቶች፡
- 1 ይዘትንመሠረትያደረገአከፋፈል።
- የስብከት ዓይነት በይዘታቸው በሦስት ይከፈላሉ። እነርሱም
- 1. ትምህርት ፡-
- በእውቀት ላይ የተመሠረተ
- ተከታታይነት ያለው
- በማስረጃ የተደገፈ
- ማብራራትን መተርጉምን፣ ማመሥጢርን የሚጠይቅ

2. ትምህርታዊ ስብከት፡-

- በጥምረት የሚስጥ
- መነሻው ትምህርት መድርሻው ስብከት የሆነ
- ማስረጃ በመስጠት ሰውን ወደ ፈጣሪው የሚያቀርብ
- እውቀትና ሕይወት በአንድ ጊዜ የሚያስጨብጥ

3. ስብከት ፡-

- ቀለል ባለ አገላለጽ የሚቀርብ
- ማስረዳትና ማሳየት ላይ የሚያተኮር
- የሰውን ልቡናና አእምሮ መማረክ እና መግዛት የሚችል

- **2b**ትምህርትአቀራረብ

  2 ታሪካዊ /Historical/
- ይህ ዘዴ አብዛኛውን ጊዜ በበዓላት ቀን የምናስተምርበት መንገድ ነው። በየበዓላቱ የዕለቱ ስንክሳር፣ ገድል፣ ድርሳን ይነበባል፣ ይተረካል። ሰባኪውና የስብከቱ ቦታ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እንደመሆኑ እነዚህን አስቀድሞ አንብቦና አጥንቶ ለምእመናን ማስተማር ይጠቅበታል።

2. ሰባኪው ሕዝቡን በሚመጥንና በማያስለች መልኩ ቀላልና ግልጽ በሆነ አቀራረብ ሰዓት መጥኖ ርዕስ መርጦ ምእመናን ከታሪኩ ተነስተው በሕይወታቸው ላይ ትርጉም እንዲኖራቸው ወደ ሕይወት በመቀየር ማጠቃለያውን ስብከት አድርጎ መጨረስ ማለት ነው።

- ነገረ ሃይማኖት /Dogmatic/
- ከስብከቶችሁሉ ጠጣርና ከባድ የሚባለው የስብከት ዓይነት ነው። ይህን ትምህርት ለማስተማር ሰባኪው የሚከተሉትን ነጠቦች ማስታዋል ይጠበቅበታል።
- ሀ. አንድ ነጥብ ላይ ብቻ ማተኮር
- ለምሳሌ፡- ሀልዎተ እግዚአብሔር ፣ ምሥጢረ ሥላሴ...
- ለ. በሚገባ ማብራራት፡- ሊያስተምር የፈለገውን ነጥብ በሚገባ ማብራራት ይኖርበታል።

- የሚያበራራባቸው ዘዴዎችም፡-
- ምሳሌዎችን በማንሳት፡- ምሥጢረ ሥላሴን ማስተማር ቢፈልግ
- በፀሐይ፣ በእሳት፣ በሰው መስሎ ማስተማር
- ስለ እመቤታችን አማላጅነት፡- የበላኤሰብን ታሪክ በማስታወስ መተረክ
- ለትምህርት አስረጂ ጥቅሶችን በማንሳት
- የሊቃውንትን ብሒል በመጠቀም

- ባለ አንድ ሐረግ ስብከት
- ባለ አንድ ሐረግ ስብከት የሚባለው ሰባኪው ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሐረግ መዝዞ ያንን ተመርኩዞ የሚሰጥ ትምህርት ነው። ለምሳሌ ‹በፈተና የሚጸና የተባረከ ነው› / ያዕ 1፡12/ ብሎ ከተነሣ፡-
- የፈተናን ምንነት
- የፈተናን ዓይነት
- ፈተና የሚመጣባቸውን መንገዶች
- ፈተናን እንዴት ማለፍ ይቻላል)
- በፈተናው ጸንተው ያለፉ ቅዱሳን ሰወችን ታሪክ እያነሣ ከዘመኑና ከሰው ሕይወት ጋር በማዋሃድ በሰፊው ማስተማር ነው። ‹አንደ ሐረግ ሲሰቡ ድር ይሰበስቡ› እንዲሉ።

- ስብከተ ወንጌል ሲዘጋጅ ታሳቢ የሚደረግ
- **4.1.** ሕዝብንማወቅ፡-
-

  ስብከተወንጌልንለአንድሕዝብለማስተማርየሕዝቡንማንነትማወቅየ
  ስብከትወንጌልመመሪያነው።
  አንድሰባኪየሕዝቡንማንነትሳያውቅየሚሰጠውየመግባርምሆነየቃል
  ትመህርትከተሰባኪውሕይወትጋርመዋሐድአይችልም።ሰለዚህ ሰባኪ
  በተቻለ መጠን የሚያስተምራቸውን/ የሚሰብካቸውን ሰዎች
  ባሕልንማወቅና ማጥናትቋንቋን፤ የሃይማኖታዊዳራ፤
  የተሰባክያኑየእውቀትደረጃ፤ የኑሮመጠናቸውን፤
  በአካባቢውያሉአስተሳሰቦች ወዘተ በተቻለው መጠን ማወቅና
  መረዳት ይኖርበታል።

- የስብከትቦታዎችን ማወቅ ፡-
- መቼም ቢሆን የስብከት ማእከላዊ ቦታ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ናት። በዚህ በተጨማሪ የምሥራቹን ወንጌል ወደ ሕዝበብ ጆሮ ለማድረስ ምቹ ቦታዎች አጎጣሚዎችን መጠቀም አለበት።

1.በሃዘን ቤት፡-

- በለቅሶ ቤት የማገኙ ወኖች ሃዘን ልናቸውነ የሰበረባቸው፣መጽናትን የሚፈልጉ ናቸው። ሃዘንተኞች ምትንና ሕየወትን፣ጽድቅንና ኩነኔን፣ የማያስቡበት ምቹ አጋጣሚ ነው። በዚህ ቦታ ሰባኪው፡-
- ሃዘንተኞችን ማጽናናት፡-
- ተስፋ ተንሣኤን ማሳየት ዮሐ. 11÷25
- የሁለተኛውን ዓለም ኑሮ ማሳየት 2ቆሮ. 5÷1
- ሞት የሥጋ ባሕርይ መሆኑን መንገር መዝ 88÷48

- በሠርግ ቤት
- በሠግ ቤት የሚገኘው ሰው ሁሉ ከርሰቲያን አይለም። የተሰበሰበውም ቃለ እግዚአብሔር እማራለሁ ብሎ አይደለም። በዚህ ሰአት ሰባኪው፡-
- አዲስ ተጋቢዎች (የዐለቱን ሙሽሮች)
- ያላገቡትን
- በትዳር ውስጥ ያሉትንም አንድ የሚያደርግ ስብከት መሰበክ ይጠበቅበታል።

- በማረማያ /ውህኒ/ ቤት፡-
- በወህኒ ቤት የታሰሩ ሁሉ ወንጀለኞች አይደሉም
- ወንጀል ሰርተው፣ኃጢአት መሆኑን አውቀው የሚጸጸቱ አሉ
- ከታሰሩበት ቦታ ሌላ ወንጀል የሚሰሩም አሉ
- ሠስርቆት ተግባር የሚፈጽሙ
- እርስ በእርስ ሚደባደቡ
- ግቢ ሰዶም የሚፈጽሙ አሉ

- 3 . Prapred ምንጊዜም ወደ ማስተማር ከመግባቱ በፊት የተዘጋጀ መሆን አለበት
- ስለተዘጋጀበት ሲያስተምር የተወሳሰበ አይሆንም
- ባረባ ነገር ስአት አያባክንም ስለተዘጋጀ ሲጀምርም ሲጨርስም በስአቱ ነው አንዳንድ ሰባክያን 20 ደቂቃ ለማስተማር ተሰጥቶት 8 ደቂቃውን በማስተዋወቅ ይጨርሳል
- በሚያስተምርበት ጊዜ ሁሉንም ይቆጣጠራል ማን እየተከታተለ ነው ማንስ እያንቀላፋ ነው የሚለዉን በደንብ ይከታተላል
- 1ኛ ጴጥ 3 ፡ 15 ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ ።

- 4. positive ቀና አመለካከት መምህር ለተማሪውም ለሚያሰተምረውም ነገር ቀና የሆነ አመለለካከት ሊኖረው ይገባል።
- See the glass as half full መመህር ሁሌም ማየት ያለበት ያለውን ነገር ነው ከቀና አመለካከት ነው መነሳት ያለበት
- የሚያመሰግንና እውቅና የሚሰጥ መሆን አለበት
- ማስተማር ያለበት በተማሪወቹ የማወቅ ደረጃ ነው
- ትምህርት ማስተማር ማለት መልካምና ቀና አመለካከትን ለተማሪወች ማጋባትና እርስ በእረሱ እንዲረዳዱ ማድረግ ነው
- ኢሳ 57፡ 2 በቅንነት ተየሄደ በአልጋዉ ላይ ያርፋል
- ምሳ 28 ፡ 18 በቅንነት የሄደ ይድናል በጠማማነት የሚሄድ ግን ፈጥኖ ይወድቃል

- ጨለማውን ከምታማርር አንድ ጊዜ ሻማ አብራ የሚለውን አባባል መፈፀም ያስፈልጋል ሻማ ስናበራ ከጨለማው ጋር ምንም ግብግብ ሳንገጥም ጨለማው በራሱ ጊዜ ይለቃል
- እኛ ሰወችን በትጋት ማስተማር ስንጀምር ሌሎቹ ያስተማርናቸው ወይም የለኮስናቸው ሻማወች ጨለማውን ያስለቅቁታል።
- ቀናነት ለማንኛውም ሰው አትራፊ ነው ያንዳንዶሰው አይን ጥቁር ነጥብን እንጂ መልካሙን ነገር ዐይመለከትም ክፉን እንጂ መልከሙን አያይም
- ኢሳ 57፡ 7 የምስረች የሚናገር ሰላምንም የሚያወራ እርሱ እጂግ ያማረ ነው
- ሉቃ 2፡ 10 ሀዲስ ኪዳን የተጀመራው የምሰራች በሚናገር መልአክ ነው

- 5. hold high expectation ለሁሉም ተማሪወች ትልቅ ግምት መስጠት ሁሉም ትልቅ ደረጃ እንደሚደርሱ ነው የሚገምተው የሚመኘው
- ትልቅ ደረጃ መሰጠት
- ሁሌም የተሻለ ነገር እንዲሰሩ ይከታተላል ያበረታታል
- በራስ መታመመን እንዲፈጥሩ ያደርጋል
- ለምሳሌ ቅዱስ ጴጥሮስ እኔም በባህር ላይ እንድመጣ ና በለኝ ሲለው ጌታችንም ና አለው እንጅ አንተማ አችልም አላለውም ሲመጣግን መሰጠም ሲጀምር ለምን ተጠራጠርክ ጅምርህ መልካም ነበር አትጠራጠር አለው
- ኢሳ 35 ፡3 የደከሙትን እጆች አበርቱ የላሉትንም ጉልበቶች አፅኑ
- ሰወ ጠሚሳበው የሚያስበውን ያክል ስለሆነ

- 6. creative የፈጠራ ችሎታ ያለው መሆን አለበት
- አለባበሱ አረማመዱ ሁሉ ሊያሰተምር ይገባል 2ኛ ቆሮ 3፡ 3 የእኛስ መጽሀፎቻችን እናንተ ናችሁ... ትታወቃላችሁም ሰውም ሁሉ ያነብባችኋል...
- መምህር ህያው መፅሀፍ ቅዱስ ወይም ተንቀሳቃሽ ቤተክርስቲያን ነው ምክንያቱም ምሳሌ የሚደርገውና ተማሪወቹ ሁሉንም የቅድስና ስራወች የሚገለጥበት ነውና
- ተማሪወቹም ተሰጦዋቸውን እንዲያሳዩ የበኩሉን ጥረት ያደርጋል
- ትምህረቱ በቀላሉ እንዲደርስ በሚያስተምረበት ክፍል ቴክኖሎጅን በአግባቡ ይጠቀማል

- 6. fair ሁሉንም ተማሪረወች በእኩል የሚመለከት የማያዳላ
- ለሁሉም ተማሪወች እኩል እድል የሚሰጥ
- ለሁሉም ተማሪወች እኩል ማስረዳት
- ለሁሉም ተማሪወች እኩል መገኘትና ለሚጠየቀው ጥያቄ እኩል ግልፅ አድርጎ የመመለስ ልምድ ሊኖረው ይገባል
- ማዘዝም መንከባከብም ካለብን እኩል መሆን አለበት
- ሁሉም ተማሪወች በተመሳሳይ ፍጥነትና ጥራት እንደማይዙ መረዳት መቻል አለባት የተሳሳተ ፍቅር ማሳየት የለብንም ለመሆኑ የተሳሳተ ፊቅር ምንድነው?

- 7. display a personal touch ለተማሪ ከተምህርት ክፍለጊዜው ውጭም መልካም የሆነ ግንኙነት መፍጠር
- ተማሪወችን በግል ማግኘት
- በክፍልም ዉስጥ የግል ልምዳቸውን እንዲገልፁ እድል መስጠት
- ፍላጎታቸው ምን እንደሆነ መወቅና ፍላጎታቸውን በተቻለ መንገድ ለማሟላት ጥረት ማደረግ
- ተማሪወቹን በዉይት ጊዜያቸው በጸሎት ጊዜያቸው መጎብኘት

8. Cultivate a sense of belonging ምቹ ነገርን መፍጠር

. እንደቤተሰብ እንዲያዩን ማድረግ

. ተማሪወቹ መምህሩ ማሰተማር ህይወቱ እንደሆነ እንዲያወቁ ማደረግ

. የተመቸ የመማር ማስተማሪያ ቦታ ማዘጋጀት

. በአካባቢው የሚረብሽ ሰሜትን የሚሰርቅ ድምፅ መኖር የለበትም

. ከፍትፍቱ ፊቱ እንደሚባለው ከምንም በፊት መምህሩ ጥሩ ፈገግታ ጥራ አቀባበል ሊኑረው ይገባል መምህሩን ከወደዱት ትምህርቱን የሚከብድ ቢሆንም እንኳን ይወዱታል መምህሩን ከጠሉት ግን ትምህርቱ ምን ቀላል ቢሆን ይጠሉታል

- 9. ብልህና ርህሩህ መሆን አለበት
- መምህር ልቡ ስስ ጀሮው ትልቅ አይኖ ሰፊ መሆን አለበት
- ብልህ መሆን ሲባል ሰውን በፍቅር መሸነፍ ማለት ነው
- ብልህ ሰው የባልንጀሮቹን ቁጥር ሲያሳድግ ሰነፍ ሰው ግን ምርጥ ባልነጀሮቹን ያጣል
- ቅዱስ የሆንስ አፈወርቅም ይህን አስመልክቶ የጠላት ማስወገጃ መንገድ እሱን ወዳጅ አድረገህ በመቀየር ነው።
- 1ሳሙ 25 ፡32-33 የናባል ሚስት አቢግያ ባለቤቷን ከሞት ያዳነችው በጥበብ ነው

- 10ኛ ትግስተኛ
- መምህርና መሪ ትግስተኛ መሆን ይኖርታል ዳዊት ሳኦል ሊገለው ባለ ጊዜ በትግስት ነው ያሸነፈው 1 ሳሙ 26 ሳኦል በእጁ ወድቆ ሳለ አልገደለውም በትእግስት አሸነፈው እንጅ
- ሲሳካላችሁ ሰው ሲወዳችሁ በቅናት ሊገድሉ የሚደርሱ ሰወች ሊነሱ ይችላሉ ነገር ግን መምህር በትግስት ነው የሚያሸነፈው
- ምሳ 25 ፡15 በትዕግስት አለቃ ይለዝባል የገራም ምላስ አጥንትን ይሰብራል
- ዕብ 12 ፡ 2 የእምነታችን እራስና ፈፃሚውን ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን እሩጫ በትግስት እንሩጥ
- በማህፀን ያለ ሽል ከመወለዱ በፊት ብዙ ወራቶችን እንደሚፈልግ ሁሉ መንፈሳዊው ሽልም ያለጊዜው እንደሚወለድ ያውቃል ስለዚህ በትእግስት ይጠብቃል ። አዝመራም እለቱን ተዘርቶ እለቱን አይታጨድም ማረምና መንከባከብ ያስፈልጋል።

- ተዐግሡ ወአጽንኡ ልበክሙ ቃለ ህሱመ ኢታውጽኡ እምአፉክሙ ዘእንበለ ይእርብ ጸሐይ አቁርሩ መአተክሙ ‹‹ታግሡ፣ ልባችሁንም አበርቱ፤ ክፉ ቃል ካፋችሁ አይውጣ። ፀሐይም ሳትጠልቅ ቁጣችሁን አብርዱ፣ ይቅር ተባባሉ።›› ከዚህ እንደምንረዳው ትዕግሥት ብርታት ነው ለምንም ነገር በቀላሉ እጅ አለመስጠት ነው። ድኅነትም ድልመንሳትም ያሉት በትዕግስት ውስጥ ነው። ያለ ትእግስት ምንም ነገር ጀምሮ መፈጸም ከባድ ነው።

- 11ኛ ትሁት መሆን አለበት
- ሉቃ 14 ፡ 7-11 ማንም ለሰርግ ቢጠራህ አስቀድመህ በከበሬታ ወንበር አትቀመጥ ምናልባት ከአንተ ይልቅ የከበረ ተጠርቶ ይሆናልና አንተንም እሱንም የጠራ ጋባሹ መጥቶ ለዚህ ስፍራ ታውለት ይልሃል ያንጊዜ እያፈርክ በዝቅተኛ ቦታ ትሆናለህ ... ብሎ በምሳሌ ጌታችን ያስተማረው ደቀ መዛሙረቱ ለማስተማር ሲሸቀዳደሙ በማየቱ እነደሆነ ነው የሚነገረው
- ማቴ 20 ፡ 26 ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የሁሉ አገልጋይ ይሁን ይህንን ትህትና ማሳየት መቻል አለብት
- መስተማርን የሥጋዊ ክብር መፈለጊያ መድረግ አያስፈልግም ክብር እንደ ጥላ ሲሸሿት የምትርቅ ሲርቋት ደግሞ የምትቀርብ ናትና

- የማቴ 23፡12 ዘአትሐተ ርእሶ ይትሌአል ወዘ አልአለ ርእሶ ይቴህት ራሱን ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ ከፍ ክፍ ይላል ራሱን ከፍ ክፍ የሚያድርግ ደግሞ ዝቅ ዝቅ ይላል። አባቶቻችን ምድር ከዚህ በታች ዝቅ የማትለው እስከመጨረሻው ዝቅ ስላለች ነው ይላሉ። ሌላው ፀሐይ በደንብ የምታሞቀው ዝቅ ያለውን ነው። ከፍ ሥትል ትቀዘቅዛለህ ስለዚህ ላለመቀዝቀዝ ራስህን ከፍ አታድርግ። ከፍ አትበል በረዶ ትሆናል።

- አባ እንጦንስ ስለ ትህትና እንዲህ በማለት ተናግረዋል። ‹‹ወጥመድ ከሰማይ ወደ ምድር ሲወድቅ አየሁ ከዚህ ወጥምድ ማን ይድናል ብይ እግዚአብሔርን ስጠይቅ ከዚህ ወጥመድ የሚድነው ራሱን ዝቅ ያደረገ ብቻ ነው አለኝ።›› ስለዚህ ትህትና ከፍ ከፍ የምንልበት ብቻ ሳይሆን ሰይጣን ሰወችን ለማጥመድ ከሚያዘጋጀው ወጥመድም የምንድንበት መንገድ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ትህትና ከእግዚአበሔር ትእዛዛት አንዱ ነው። ማቴ 11:9 ‹‹ከእኔ ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ተሁት ነኝ›› ብሎ እንዳዘዘን ሰው ሁሉ መላ ዘመኑን በትህትና ሊኖር ይገባል።

- ምንተ ትትሌአል ኦ ሰብዕ እንዘ ጽቡር አንተ ወኩስህ ወምንተ ትትኔፋህ ወፈድፋደ እምደመናትኒ ትትሌዓል ጠይቅ ፍጥረተከ ከመ መሬት አንተ ወሐመድ እምድህረ ንስቲት ለሐመድ ትግብዕ ይእዜሰ ትትኬበር እምድኅረ ንስቲት ለእጼአት ምንተ ክሳደከ ታሌዕል እምድኅረ ንስቲት ትሴአር ከመ ዘያቴህት ርዕሶ ተመስል እስመ ዘያቴህት ርእሶ የዓቢ ወይከብር ሰብአ በመንግሥተ ሰማያት። ሰው ሆይ አፈርና ትቢያ ስትሆን ራስህን ከፍ የምታደርገው ለምንድን ነው? ለምንድነው በትእቢት የምትወጣጠረው? ከደመና በላይ ከፍ ትላለህን? እስኪ ተፈጥሮህን መርምር /ጠይቅ/ አፈርና አመድ እኮነህ።

- 12. ማስተማር የእዳ ክፍያና ግዴታ ነው
- ቅድስት ቤተክርስቲያን እኛ በጀትም አስተማሪም ሁና አስተማራለች ስለዚህ ይህንን እዳ ልንከፍል ያስፈልጋል
- ዮሐ 4፡ 29 ..ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሠው ኑና እዩ
- ማቴ28 ፡ 19 ሁሩ ወመሀሩ
- ስለዚህ ማስተማር ግዴታ ነው ይሄንን ግዴታ ማወቅና ማገልገል ይጠበቅብናል

- 13. ጥሩ የመናገር ችሎታ ሊኖረን ያስፈልጋል
- አድማጩ ማነው
- ለእነሱ የሚመጥን ነገር ምንድነው
- የሚፈልጉት ምንድነው
- ንግግሩ ኦርቶዶክሳዊ ላህይ ያለው መሆን አለበት።
- ሰባኪው የቤተ ክርስቲያን መቃን የመታው የቤተ ክርስቲያንን ቋንቋ በሚገባ የሚያውቅ መሆን አለበት።
- ጸያፍ የሆኑና ኦርቶዶክሳዊ ያልሆኑ ቃላትን መጠቀም የለበትም።
- የማይመጥኑ ወይም ለአድማጩ ከባድ የሆኑ ቃላትን መጠቀም የለበትም

- 14. ፍላጎት መኖርና ሙያውን መውደድ
- ሙያውን ስንወደው እንደ ቅዱስ ያሬድ ሰወችን በምንፈልገው ሰረገላ ጨነን ሰወችን ወደምንፈልገው የስራ መስክ መውሰድ እንችላልን
- ከምንም ነግር በፊት ፍላጎት ሊኖረን ያስፈልጋል
- ፍላጎት ሳይኖር መስራት አይቻልም ቢጀመር እንኳን ዘለቄታ የለውም
- ነቢይነትን ከክህነት ጋር አስተባብሮ ይዞ የነበረው ነቢየ እግዚአብሔር ህዝቅኤል እግዚአብሔር ለልዩ ተልእኮ ሲጠራው መጀመሪያ የተሰጠው መመሪያና ትዕዛዝ ተነስቶ በእግሩ እነዲቆም ነበር እርሱም በተሰጠው መመሪያ መሰርት ተነስቶ በእግሩ ቆመ ህዝ 2፡1

- ዘፀ 3፡ 15 ሙሴ ልሂድና እፀዋቷ እንዴት እንደተቃጠልች ልይ ማለቱ መንፈሳዊ ምስጢርና መንፈሳዊ እውቀት እንደሚያገኝ የሚገልፅ ነው እንደሚባለው መመህርም ይህንን ጉጉት በተማሪወች ላይ የሚፈጥር መሆን ይጠበቅበታል

- ከዚህ ላይ እንደምንረዳው ከመንም ስራ በፊት መነሳት ይቀድማል መነሳት ሲባል የአካል መነሳትን ብቻ ሳይሆን የልቡና መነሳትንም ያጠቃልላል ስለዚህ ከምንም በፊት ከአልጋ መውረድ በእግር መቆም ያስፈልጋል። የአልጋላይ ጉዙ ወደ ሀኪም ቤትና ወደመቃብር ያደርሳል እንጅ ወደስራ ቦታ አይወስድምና ከእንቅልፍህ ንቃ፣ ከአልጋህ ውረድ፣ ወገብህንም ተጥቀህ በህይወት የሚያኖርህን ጉዞ ተራመድ።

- 15 ቁረጠኝነት ሊኖረው ይገባል
- ሮሜ 8 መኑ የሀድገነ ፍቅሮ ለክርስቶ እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ ለአላመው እስከሞት ድረስ የታመነ መሆን አለበት
- መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሃንስም ከልደት በፊት ጀምሮ በሞት እንኩዋን እንዳያቆም ያደረገው እግዚአበሔር የልቡን ቁርጠኝነት ስለሚያውቅ ነው
- እንደዚህ ቁርጠኝነት ሲኖረን እግዚአብሔርም ሀይልና ብረታቱን ይሰጠናል
- መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ እምነትህ ይሁንልህ የሚለው የልባቸውን ቁርጥ ሃሳብ ማሳወቂያ ነበር
- ማቴ 19 ፡16 የዘለአለም ህይወትን እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ
- ሉቃ 10፡ 35 በሽተኛን ለማስታመም በቁርጥ ሃሳብ የሚቀበልና ብዙ ወጭ ቢያስወጣው እንኳን ለማወጣት ቁርጥ ሃሳብ ያለው

- 16 የቅርታ የሚያደርግና በደልን የማይቆጥር መሆን አለበት
- መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትንሳኤው ጊዜ እነሳለው እንዳለ ለደቀ መዛሙርቴ ተነስቷል ብላችሁ ንገሯቸው ለጴጥሮስም ያለው የቅረታዉን ማሳየት ነው
- መምህር ምንግዜም የይቅርታ ልብ ሊኖረው ያስፈልጋል
- ማቴ 9፡ 13 እና 12፡7 ምህርትን እወዳለሁ መስዋዕትን አይደለም
- ቆላ 3፡12 የተወደደ ሰው የሚባለው ምህረት ቸርነትን ርህራሄን ትህትናን ... የለበሰ እንደሆነ ተግልጿልና መምህር ይቅርታ የሚያድርግና የሚምር መሆን ይጠበቅበታል።

- 17. ማስተማር መለወጥ ነው
- እብ 5 ፡12 ከጊዜው የተነሳ አስተማሪ መሆን ሲገባችሁ አንድ ሰው ስለእግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የህፃንነት ትምህርት እንዲያስተምራችሁ ትሻላችሁ
- ስለዚህ ማስተማር አንድ ጊዜ ነግረው የሚጨርሱት የሚያቆሙት ሳይሆን ከእንድ ደረጃ ወደሚፈለገው ደረጃ እስከሚደርሱ ድረስ በትጋት የሚከታተሉት ስራ ነው

- 18 ጠንከራ ስሜት ሊኖረው ይገባል
- በቀላሉ የማይበርድ ስሜት ሊኖረው ይገባል
- አለምልሞ መገሰፅ የሚችል መሆን አለበት ይህ ማለት አስተምሮ መምክርና መገሰፅ አለበት ማለት ነው
- ለምሳሌ ዮሐ 3 ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኒቆዲሞስን የገሰፀው ካስተማረ በኋላ ነው

- 19 ማስተማር ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር የምንገልፅበት ነው
- ዮሐ14 ፡ 23 የሚወደኝ ቢኖር ትዛዜን ይጠብቅ
- ማቴ 28 ፡19 ሁሩ ወመሀሩ ኩሎ አህዛበ ይህ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው ስለዚህ ማስተማር የእግዚአብሔር መፈፀም ነው
- እግዚአብሔርን ትወደዋለህ እገዚአብሔርን የምትወደው ከሆነ ትእዛዛቱን በማስተማር ፈፅም
- የሐ 21፡ 15 በጎቸን ጠብቅ ይህ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው በርካታ ተኩላ ያለበት ዘመን ነው
- መምህር ከምድራዊው ወደ ሰማያዊው ጫፍ እስከልጆቹ የሚደርስ መምህር ከአለማዊው የባህር ዳርቻ ወደ መንፈሳዊው ዳርቻ ይዘው የሚሻገሩ ናቸው የሚሻገሩም ጭምር እንጅ እነሱ ወደኋላ እየቀሩ ሌሎቹን ብቻ የሚያሻግሩ መሆን የለባቸውም

- 20 እግዚአብሄር በአልግሎታቸው እንዲገባ የሚፈቅዱ ናቸው
- መዝ 136 ፡ 1 እመ እግዚእግአብሔር ኢሀነፀ ቤተ ከንቶ ይፃምኡ እለ ይሀንፁ ስለዚህ እኔ ኢምንት ነኝና አንተ 30 60 100 ፍሬ እንዲያፈሩ አድረጋቸው እኔንም ድካሜን ከንቱ እንዳታስቀርብኝ እያለ ይጸልያል
- 1ቆረ 3፡7 እንግዲህ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጅ የሚተክልም ቢሆን ወይም የሚያጠጣ አንዳችም አይደለም
- ማጠጣትን መትከል ለማደጋቸው ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ እንጅ በራሳቸው እድገትን አያመጡም
- ዶክተር መድሃኒት ይሰጣል እንጅ ድህነትን አያመጣም ገንዘብ አልጋን ይገዛል እንጂ እንቅልፍን አያመጣም
- ያለእኔ ምንም ምን ልትሰሩ አትችሉም ዮሐ 1 ያለውን ያውቃሉ

- 21 መስራት ያለበትን በሰአቱ ነው የሚሰራው
- የሌባ ክፉ የሰአት ሌባ እንደሆነ ስለሚያውቅ ሰአት አይሰርቅም - የስራ ሰአት ማለቴ ነው
- 2ቆሮ 6፡2 እነሆ የተወደደው ሰአት አሁን ነው የመዳንም ቀን አሁን ነው
- መክ 12፡ 1 የጭንቅ ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አሰብ ፀሀይ ጨረቃ ከዋክብትም ሳይጭልሙ... ይህ ሁሉ ሳይመጣ በሰአቱ ስራውን የሚሰራ ነው
- ምሳ 6፡ 6 መብልዋን በበጋ መኖዋንም በመከር ትሰበስባለች ጉንዳኖች ስራቸውን የሚያከናውኑት በፕሮግራምና ውጤታማ ሊያደርጋቸው በሚችል ጊዜ ነው። መስራት ብቻውን ውጤታማ አያደርግም መቼ? የት ቦታ? በምን አይነት መንገድ? ከእነማን ጋር? የሚለው ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

- ስለዚህ መስራት ያልበንን በወቅቱ መስራትና መለወጥም መለወጥም በሚገባን ሰአት መለወጥ አለብን
- እራሳችንን ቀይረን እድገት ማሳየት ይጠበቀብናል ባለበት የሚረግጠው የተበላሸ የሴኮ ሰዓት መቁጠሪያ ብቻ ነው። እኛ ግን የምንሰራ ህይወት ያለን ለመስራትም ለመለወጥም የተፈጠርን ነን እና ከስንፍና ወደ እውቀት፣ ከክፋት ወደ በጎነት፣ ከዘረኝነት ወደ አንድነት፣ ከመቀማት ወደ መመፅወት፣ ከጥላቻ ወደ ፍቅር ወ.ዘ.ተ ተለውጠን መልካም ፍሬ አፍርተን የስሙ ቀዳሾች የክብሩ ወራሾች ያደርገን ዘንድ የአምላካችን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንለን። !!

መስበሐት

ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር ይቆየን

ጥቅምት /2011